የሰ/መ/ቁጥር 218338

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኘ

አመልካች ፡ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ነ/ፈጅ ጀማል መሀመድ ቀረቡ

ተጠሪ ፡ ብርሃን ባንክ አክስዮን ማህበር ነ/ፈ ገመቹ አለሙ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የግንባታ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ አሁን ተከራካሪ ያልሆነው ሼድ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ 1ኛ ተከሳሽ እና ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በሰኔ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ አመልካች በ2011 በጀት አመት ከሚያስገነባቸው የህንጻ ግንባታዎች መካከል ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና የመምህራን መኖሪያ ቤት በብር 286,622,093 ለማስገንባት ተዋውለናል፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ከተጠሪ ባንክ ያቀረበ ሲሆን በዋስትና ሰነዱ ላይ ለስር 1ኛ ተከሳሽ በአመልካች የሚከፈለው የቅድመ ክፍያ በተጠሪ ባንክ ገቢ እንዲደረግ ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን የስር 1ኛ ተከሳሽ የቅድመ ክፍያው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ እንዲደረግለት በማመልከቻ በጠየቀው መሰረት በቼክ ዲፖዚት አመልካች ቅድመ ክፍያውን ገቢ አድርጌአለሁ፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ብር 24,923,660.26 ቅድሚያ ክፍያ ከወሰደ በኋላ ስራውን ያቆመ በመሆኑ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስ ወይንም በውሉ መሰረት መፈጸም የሚፈልግ ከሆነ ስራውን እንዲቀጥል እና ተጠሪም በሰጠው የዋስትና ሰነድ መሰረት ገንዘቡን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ታዟል፡፡ ተጠሪ በነሐሴ 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ የሰጠው ዋስትና የሚጸናው አመልካች የቅድመ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ በስር 1ኛ ተከሳሽ

በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ቢያደርግ ኖሮ ነበር፡፡ ካልሆነ ግን የዋስትና ሰነዱ ተቀባይነት እንደማይኖረው በዋስትና ሰነዱ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሆኖ እያለ አመልካች በቅድመ ሁኔታው መሰረት የቅድመ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ ገቢ አለማድረጉ የአመልካችን ቸልተኝነት የሚያሳይ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገው የግንባታ ውል አንቀጽ 60/2 የስር 1ኛ ተከሳሽ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ማቅረብ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በግዢ መመሪያ 2002 የቅድመ ክፍያ የሚከፈለው ተመጣጣኝ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ሲቀርብ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም ተጠሪ ዋስትናው በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የስር 1ኛ ተከሳሽ እና ተጠሪ በአንድነት እና በነጠላ ብር 24,923,660.26 ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ያስቀርባል ተብሎ ክርክር ከተደረገ በኋላ የግዢ መመሪያውም ሆነ በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአመልካች መካከል የተደረገው የግንባታ ውል በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ መቅረብ እንዳለበት የሚያመለክቱ ቢሆኑም እነዚህ ድንጋጌዎች በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ ግዴታ የሚጥሉ ናቸው፡፡ ተጠሪ የግንባታ ውሉ አካል ባለመሆኑ በውሉ ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች አይመለከቱትም፡፡ በዋስትና ሰነዱ ላይ የቅድሚያ ክፍያው በተጠሪ ባንክ ገቢ ካልተደረገ የዋስትና ሰነዱ ተቀባይነት እንደሌለው ሰፍሯል፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሰነድ ሲቀርብለት ዋስትናውን አልቀበልም በማለት የቅድመ ክፍያውን አለመክፈል እየቻለ በዋስትና ሰነዱ ከተቀመጠው ውጪ በሌላ ባንክ ቅድመ ክፍያውን ከከፈለ በኋላ ተጠሪ በዋስትና ሰነዱ መሰረት ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር ቅሬታ ያቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ አላማ ባለመብቱ ክፍያ ሲጠይቅ ወዲያውኑ ክፍያ እንዲፈጸም ለማስቻል ነው፡፡ በግዢ መመሪያ ላይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ መቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ አስገዳጅ የሆነውን የግዢ መመሪያ በመቃረን በዋስትና ሰነድ ላይ ቅድመ ሁኔታ ማስፈሩን እንደመከራከሪያ ሊያነሳ አይችልም፡፡ ተጠሪ በራሱ ባንክ የቅድሚያ ክፍያው ገቢ ካልተደረገ የዋስትና ሰነዱ እንደማይጸና መግለጹ በመንግስት ንብረት እና ሐብት ላይ ብክነት የሚፈጥር ነው፡፡ የመንግስት ክፍያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ መከፈል እንዳለበት በመመሪያ ተደንግጓል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ይህንን መመሪያ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ በሚያዝያ 08 ቀን 2011 ዓ.ም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ያለቅድመ ሁኔታ መስጠቱን ለአመልካች ገልጾ አመልካችም ይህንን መሰረት በማድረግ ለስር 1ኛ ተከሳሽ ክፍያ ከፍሎ

እያለ የአመልካች ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ግራ ቀኙ ካደረጉት ስምምነት፣ ከመንግስት ግዢ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 48/1 እና ከመንግስት የግዢ መመሪያ ቁጥር 01/2002 አንቀጽ 16/26/2 አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በመጋቢት 07 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በግዢ መመሪያ እና በግንባታ ውል የሰፈሩ ድንጋጌዎች ገዢ የሚሆኑት በተዋዋዮች መካከል ነው፡፡ ተዋዋይ ባልሆነው ተጠሪ ላይ የግንባታ ውሉ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ አመልካች በተጠሪ ሂሳብ የቅድመ ክፍያው መከፈል አለበት በሚለው ካልተስማማ የዋስትና ሰነዱን አለመቀበል ይችል ነበር፡፡ የቅድሚያ ክፍያው በተጠሪ ባንክ እንዲከፈል መደረጉ የዋስትና ሰነዱ እናዲጸና የሚያደርግ ነው፡፡ አንዴ የዋስትና ሰነዱ ከጸና በኋላ ግን ተጠሪ የክፍያ ጥያቄ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ አይችልም፡፡ ያለቅድመ ሁኔታ ክፍያ ለመፈጸም የተስማማሁት የዋስትና ሰነዱ የጸና ከሆነ በኋላ ነው፡፡ የጸና ዋስትና ሰነድ በሌለበት ተጠሪ ክፍያ እንድከፍል ልገደድ አይገባም፡፡ በመሆኑም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ የስር 1ኛ ተከሳሽ ከአመልካች ጋር በገባው የግንባታ ውል ምክንያት አመልካች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ለሚከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የዋስትና ሰነድ መስጠቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የስር 1ኛ ተከሳሽ በገባው ውል መሰረት ለአመልካች ክፍያ ካልፈጸመ ተጠሪ በሰጠው ዋስትና ሰነድ ሊገደድ የሚችለው በምን ሁኔታ ነው የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው በዋስትና ሰነዱ ልገደድ የምችለው በዋስትና ሰነዱ ላይ በተገለጸው መሰረት አመልካች የቅድሚያ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ በስር 1ኛ ተከሳሽ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ሲያደርግ ነው፡፡ አመልካች ግን የቅድሚያ ክፍያውን በሌላ ባንክ ገቢ ስላደረገ በዋስትና ሰነዱ መሰረት ክፍያ የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ሆኗል በሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ በቅድሚያ ክፍያ ሰነዱ ላይ ለስር 1ኛ ተከሳሽ የሚከፍለውን ቅድሚያ ክፍያ በተጠሪ ባንክ በኩል መከፈል እንዳለበት በዋስትና ሰነዱ ላይ መገለጹን ሳይክድ በግንባታ ውሉ እና በግዢ መመሪያ መሰረት መቅረብ ያለበት በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ሰነድ ሊሆን እንደሚገባ የተመለከተ በመሆኑ የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት ስለሌለው ተጠሪ በገባው የዋስትና ግዴታ መሰረት ክፍያ ሊፈጽምልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልገውም የዋስትና ሰነዱ ቅድሚያ ክፍያው በተጠሪ ባንክ በኩል ለስር 1ኛ ተከሳሽ መከፈል እንዳለበት እየገጸ አመልካች ክፍያውን በሌላ ባንክ በኩል መፈጸሙ አመልካች በዋስትና ሰነዱ መሰረት ከተጠሪ ክፍያ የመጠየቅ መብቱን ያስቀረዋል ወይስ አያስቀረውም? የሚለው ይሆናል፡፡

አመልካች ከተጠሪ ውጪ በሆነ ባንክ ለስር 1ኛ ተከሳሽ የቅድመ ክፍያ መክፈሉ ከተጠሪ በዋስትና ሰነዱ መሰረት ክፍያ የማግኘት መብቱን ቀሪ ያደርግበታል ወይስ አያደርግበትም? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለመስጠት የቅድሚያ ክፍያ የዋስትና ሰነድ( Advance Payment Guarantee Bond) ምንነት ከሌሎች የዋስትና አይነቶች ያለዉ አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ መታየት ያለበት ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36935፣ 40186 እና 47004 (ቅጽ 13 ላይ የታተሙ)የሕግ ትርጉም ነዉ፡፡ በእነዚህ መዛግብት ላይ በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ የዋስትና ዉሎች ናቸዉ የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 47004 ላይ በተሰጠው ዉሳኔ እንደተመለከተዉ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) ማለት አንድ ሰዉ አንድን የተለየና የተወሰነ ሥራ ለሌላ ሰዉ ለመስራት ግዴታ ከገባ ይኸዉ ሰዉ በዉሉ መሰረት የገባዉን ግዴታ መፈጸም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌላዉ ሰዉ የሚያቀርበዉ ዉል ነዉ፡፡ እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ሥራ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ለኮንስትራክሽን ሥራዉ በዉሉ መሰረት መከናወን ዋስትና የሚሰጥ ሰነድ እንደሆነ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁጥር 36935 እና 40186 ላይ በተሰጠ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ሌላ ሰዉ ያለበትን የገንዘብ እዳ በገባዉ ዉል መሰረት ባይከፍል ሌላ ሰዉ እራሱ ለአበዳሪዉ እንደሚከፍል ገልጾ ራሱን ግዴታ ዉስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የተለያዩ ሕግጋትን በማጣቀስ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጓሜዎች ላይ ስለ ገንዘብ ዋስትና ሰነድ ምንነት ከቅድሚያ ክፍያ ዋስትና (Advance Payment Guarantee/Bond) እና ከመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ ጋር ያለዉ አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆነ የተመለከተ ነገር ባለመኖሩ ምንነቱን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በወጣ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 2/2 ላይ "ማገቻ(Bond) ማለት የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰዉ ለሌላዉ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸዉንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትእዛዝም ሆነ ለአምጪዉ የማይከፈልበት አንድ ሰዉ ለሌላዉ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸዉንም ሰነድ ይጨምራል፡፡"የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ ትርጓሜ መገንዘብ የሚቻለው የዋስትና ሰነዶቹ የሚሰጡት ዋናው ባለእዳ የሚፈለግበትን እዳ ወይም ክፍያ ወይም ግዴታ የገባበትን ስራ በውሉ መሰረት ባያከናውን የዋስትና ሰነዱን የሰጠው አካል ከዋናው ባለእዳ ጋር ኃላፊነት የሚኖርበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ለምሳሌ ያክል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3271 ስር ሥራ ተቋራጩ ከመስሪያ ቤቱ ጋራ ስለ ተዋዋለዉ ሥራ አስቀድሞ ገንዘብ ለመቀበል የሚችለዉ ለዚሁ አስቀድሞ ለሚከፈለዉ ገንዘብ እጅግ ቢያንስ ግማሹን መልሶ ለመክፈል የሚችል አንድ ዋስ ወይም ሌላ ዋስትና ከሰጠ በኋላ ሆኖ በዚህ መልኩ አስቀድሞ የሚከፈለዉ ገንዘብ በሥራዉ ዉል ጊዜ በተወሰነዉ መሰረት ወደፊት ሥራ ተቋራጩ ከሚፈልጋቸዉ ቀሪ ገንዘቦች ላይ ተቀናሽ የሚሆን ገንዘብ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ከተጠቃሾቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ በተለይ ከግንባታ(ከኮንስትራክሽን) ዉል ጋር በተያያዘ ሥራ ተቋራጩ ከአሠሪዉ ጋር በገባዉ ዉል መሰረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለወደፊት ሥራ ሰርቶ በየጊዜዉ ከሚከፈለዉ ክፍያ ላይ እየተቀነሰ

ለአሰሪዉ ተመላሽ እንደሚያደርግ ወይም እንደሚከፍል በመስማማት አስቀድሞ የሚቀበለዉ ገንዘብ ቅድሚያ ክፍያ የሚባል ሲሆን በዚህ መልኩ ሥራ ተቋራጩ ከአሠሪዉ በቅድሚያ የሚቀበለዉን ገንዘብ በዉሉ በተወሰነዉ ጊዜ የግንባታ ሥራ ሰርቶ ከሚከፈለዉ ገንዘብ ላይ በየጊዜዉ እየቀነሰ ለአሰሪዉ(ለከፋዩ) ካልመለሰ ወይም መመለስ ካልቻለ ሌላ ሶስተኛ ወገን በዚህ መልኩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ለሥራ ተቋራጩ የተሰጠዉን ገንዘብ ወይም ሥራ ተቋራጩ ሳይመልስ የቀረዉን ገንዘብ እከፍላለዉ ብሎ ራሱን ግዴታ ዉስጥ የሚያስገባበት ዉል ደግሞ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉል (Advance Payment Guarantee/Bond) እንደሚባል ነዉ፡፡

ስለሆነም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ዓላማዉ ዋናው ባለእዳ እዳውን መክፈል ባልቻለ ጊዜ የዋስትና ሰነድ ሰጪው እዳውን እንዲከፍል ለማድረግ ነው፡፡ በተግባር እንደሚሰራዉ ም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond)፤ የቅድመ ክፍያ ዋስትና(Advance Payment Guarantee/Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ሰነድ/ የዱቤ ግዢ ክፍያ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) የሚሰጥበት ዓላማ ተመሳሳይ ነዉ፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 36935፣ 40186 እና 47004 (ቅጽ 13 ላይ የታተሙ) በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ የዋስትና ዉሎች ናቸዉ ተብሎ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንደተሰጠዉ ሁሉ በሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የተወሰደዉ ገንዘብ ለአሠሪዉ የሚመለስ ስለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሚሰጥ የቅድሚያ ክፍያ ማገቻ ሰነድም (Advance Payment Guarantee/Bond) በሰነድ ሰጪዉና በተጠቃሚዉ(ቅድሚያ ክፍያ በከፈለዉ አሠሪ) መካከል የዋስትና ዉል የሚያቋቁም ሰነድ በመሆኑ በእነዚሁ የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዛ ሰነድ ነዉ፡፡

የዋስትና ሰነዱ የዋስትና ዉል ቢሆንም ከሌላዉ ዋስትና ልዩ የሚያደርገዉ ባህርይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ዋስ የዋስትና ግዴታ ዉስጥ የሚገባዉ ለራሱ ጥቅም በማግኘት አይደለም፡፡ በባንኮች ወይም በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚሰጥ የዱቤ ግዢ ክፍያ ዋስትና፤ ቅድመ ክፍያ ዋስትና፣ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ...ወዘተ ግን ባንኮች ወይም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የንግድ ድርጅቶች በመሆናቸዉ ዋስትናዎቹን ሲሰጡ ዋስትና እንዲሰጠዉ ከሚያመለክተዉ ሰዉ ላይ ባላቸዉ አሰራር መሰረት ዋስትና የተሰጠው አካል ዋስትና የተሰጠበትን ምክንያት በአግባቡ እያከናወነ መሆኑን መቆጣጠር እና መከታተል የሚያስችል ስርአትን በዋስትና ሰነዱ ላይ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ በዋስትና ሰነዱ ላይ ከተመለከተዉ ሁኔታ ዉጭ የዋስትና ሰነዱ ተጠቃሚ የክፍያ ጥያቄ ባቀረበበት በማንኛዉም ጊዜ ክፍያ መፈጸም አለባቸዉ የሚባል ከሆነ በባንኮች፣ በስተጀርባቸዉ ባሉት ባለአክሲዮኖች፣ ገንዘብ አስቀማጮች ላይ ብሎም በአገር ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት ስለሚደርስ የዋስትና ሰነዱ ተጠቃሚ የክፍያ ጥያቄዉን በዉሉ በተመለከተዉ ሁኔታ ከፈጸመ በኋላ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ተጠሪ በሰጠው ለክርክሩ መሰረት በሆነው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ላይ ተጠሪ በሰነዱ ሊገደድ የሚችለው ወይም አመልካች በሰነዱ ክፍያ የመጠየቅ መብት የሚያገኘው አመልካች ለስር 1ኛ ተከሳሽ የሚከፍለውን ቅድሚያ ክፍያ

በተጠሪ ባንክ በስር 1ኛ ተከሳሽ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ሲደረግ ብቻ መሆኑን በዋስትና ሰነዱ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ በዋስትና ሰነዱ ላይ እንዳይካተት የሚከለክል ሕግ እስከሌለ ድረስ ተጠሪ በሰነዱ ላይ ይህንን ግዴታ የማስቀመጥ መብት አለው፡፡ አመልካች የግዢ መመሪያ እና የግንባታ ውሉ ተጠሪ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ እንዳይሰጥ ይከለክለዋል በሚል ተከራክሯል፡፡ በእርግጥ በአመልካች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገው የግንባታ ውል የስር 1ኛ ተከሳሽ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረት የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ሕ/ቁጥር 1731/1 መሰረት የውል አስገዳጅነት በተዋዋይ ወገኖች ላይ ብቻ የተገደበ ስለሆነ የግንባታ ውሉ ድንጋጌዎች ተዋዋይ ያልሆነውን ተጠሪን ሊያስገድዱ አይችሉም፡፡ በሌላ አባባል የዋስትና ሰነዱ ከግንባታ ውሉ የተለየ እራሱን የቻለ ሰነድ በመሆኑ የስር 1ኛ ተከሳሽ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ሰነድ ለማቅረብ የውል ግዴታ መግባቱ ተጠሪ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ እንዳይሰጥ የሚከለክለው አይደለም፡፡ በግዢ አዋጅ እና በግዢ መመሪያ ላይ የቅድሚያ ክፍያ ተቀባዩ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ሰነድ ለአሰሪው የማቅረብ እና አሰሪውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የዋስትና ሰነድ ሊቀርብለት እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም የድንጋጌዎቹ ተፈጻሚነት በገዢ እና በሻጭ ማለትም በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአመልካች ላይ እንጂ የሻጭ እና የገዢ ግንኙነት በሌለው በተጠሪ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይልቁንም አመልካች በስር 1ኛ ተከሳሽ የቅድሚያ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ በኩል መክፈል እንዳለበት ካልሆነ የዋስትና ሰነዱ የጸና ሊሆን እንደማይችል የሚገልጽ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ሲቀርብለት የስር 1ኛ ተከሳሽን የውል ግዴታህን አልተወጣህም በሚል የዋስትና ሰነዱን አልቀበልም ማለት ወይም ተስተካክሎ እስኪመጣ ክፍያ አልፈጽምም ማለት ወይም በቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ ላይ እንደተገለጸው ለስር 1ኛ ተከሳሽ የቅድመ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ በኩል መክፈል እየቻለ በሌላ ባንክ በኩል ክፍያውን ከፈጸመ በዋስትና ሰነዱ መሰረት ክፍያ የመጠየቅ መብቱን እንደተወ የሚያስቆጥር ይሆናል፡፡

የአመልካች ሌላው ክርክር በኢትዮያ ንግድ ባንክ በኩል ክፍያ የፈጸምኩት መመሪያ ስለሚያስገድደኝ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካች ክፍያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ እንዲፈጽም የሚያስገድደው መመሪያ ካለም የስር 1ኛ ተከሳሽ የዋስትና ሰነዱን ሲያቀርብለት ክፍያ በተጠሪ ባንክ በኩል መፈጸም አለበት የሚል በመሆኑ የዋስትና ሰነዱን አልቀበልም ማለት ነበረበት፡፡ ክፍያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መከፈል እንዳለበት የሚገልጽ መመሪያ እያለ አመልካች በተጠሪ ባንክ ቅድሚያ ክፍያ መከፈል እንዳለበት የሚገልጽ የዋስትና ሰነድ ሲቀርብለት መቀበሉ መመሪያውን የጣሰው እራሱ አመልካች መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን መመሪያ በመጣስ ውሳኔ ሰጥቷል በሚል አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል የስር 1ኛ ተከሳሽ በግንባታ ውሉ እና በግዢ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የቅድሚያ ክፍያ የባንክ ዋስትና ሰነድ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት አከራካሪ አይደለም፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ባንክ ያቀረበው የዋስትና ሰነድ ግን የዋስትና ሰነዱ ተቀባይነት የሚኖረው ወይም የጸና የሚሆነው አመልካች ለስር 1ኛ ተከሳሽ ቅድሚያ ክፍያውን በተጠሪ ባንክ በኩል ሲከፍል መሆኑን የሚገልጽ እና ሰነዱ የጸና የሚሆንበትን ሁኔታ የያዘ የዋስትና

ነው፡፡ ይህም የስር 1ኛ ተከሳሽ በግንባታ ውሉ እና በግዢ ሕጉ መሰረት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ሰነድ የማቅረብ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ አመልካችም የዋስትና ሰነዱ ሲቀርብለት በውሉ እና በግዢ ህጎች መሰረት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋስትና ሰነድ የቀረበለት መሆኑ አጣርቶ ሰነዱን የመቀበል ሀላፊነት እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ አመልካች ይህንን ሃላፊነቱን በአግባቡ ሳይወጣ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዋስትና ሰነድ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ ሁኔታውን ተከትሎ ማለትም በተጠሪ ባንክ በኩል ለስር 1ኛ ተከሳሽ ቅድሚያ ክፍያውን ባልከፈለበት ተጠሪ ሊገደድበት የሚችል የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተጠሪ አንጻር የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላላገኘን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 195566 በመስከረም 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

አለበት